# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 3 ቁጥር 1 መስከረም ፫ ቀን ፪ ሺህ ፰ ዓ.ም.


## ጎሕ የነቃች አንቂ

*(የጎሕ መጽሔት 41ኛ ዓመት ልደት ምክንያት በማድረግ)*

*“በአገራችን እስከ የካቲት ወር ንቅናቄ ድረስ የኢትዮጵያ ዜና ማሰራጫዎች ውድቅ የሆነውን የአድሃሪ መንግሥት ጥቅም ለመጠበቅና ክብር ለማሞካሸት ሲባል በሞኖፖል ተይዘው ቆይተዋል።*

*ጋዜጠኞች በአወናባጆች የተጽዕኖ ቀንበር ሥር ስለነበሩ በግልጽ አስተያየት ሊሰጡባቸው በሚችሉት አርዕስተ ጉዳዮች ላይ በመተቸት በትክክለኛ ዜና ያንባቢውን ፍላጐት አላረኩም ነበር።*

*ለዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ምክንያት የሆነው አቅዋም ተገንድሶ በስፍራው አዲስ አስተሳሰብና የመንፈስ ለውጥ አሁን ተተክቷል። ለዚች ጎሕ ብለን ለሰየምናት መጽሔት መመሥረት መነሾ የሆነው በጋዜጣ ዓለም በተሠማራነው ዘንድ ለውጡ የሚያሳየው ጎሕ እያንጸባረቀ የሞራል ብርታት አድሎን ይህን የግል መጽሔት ለማቋቋም ተነሳን።”* ጎሕ መጽሔት ጥቅምት ወር ሺ፱፻፷፯ ዓ.ም. ፩ኛ እትም።

ለመላው ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን እንኳን ለአዲሱ ዓመት 2008 ዓ.ም. በሰላም አደረሳችሁ እንላለን ከ«ያ ትውልድ ተቋም»። የ«ያትውልድ ተቋም» የመረጃ ምንጭነታችንን እያዳበርን በአዲሱ ዓመት በመስከረም አደይ አበባ ታጅባ፣ በመስከረም ፀደይ አንፀባርቃ፣ የዕውቀት ብርሃኗንና ትዝታዋን ልትረጭ የዛሬ 41 ዓመት በማለዳ ጎሕ ሳይቀድ ጎሕ ብቅ ብላለች። ልክ የዛሬ 39 ዓመት መስከረም ወር የመጨረሻ ዕትሟን አስነብባ ያሸለበችውን ጎሕ ዛሬ ከፍ ብላ ድምጿን እንድታሰማ፣ ትዝታዋን እንድትዘራ፣ አታጋይነቷን እንድትመሰክር ያ ትውልድ ድረ ገጽ (www.yatewlid.com, www.yatewlid.org) ከተራራው ጫፍ ብቅ አድርጓታል።

በጥቅምት ወር 1967 ዓ.ም. የመጀመሪያ እትሟን ለአንባቢያን ያቀረበችው ጎሕ 1967 ዓ.ም. እና 1968 ዓ.ም. “ኪነት ለመደቧ” እንዲሉ ከሠፌው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጐን ቁማ አታግላለች፣ አደራጅታለች፣ አንቅታለች፣ አስተምራለች…። በወቅታዊና ሀገራዊ ጉዳዮች ትንታኔዋን ትምህርታዊ በሆነ አቀራረብ ዘግባ ለንባብ አብቅታለች። የዕድገት በህብረት ዘማቾችን ከቤተሰብ አገናኝታለች። በ”ኪነ ጥበብ” አምዱ ውብ ግጥሞችን ቅላጼ በተሞላው ዜማዎቿ ገጥማለች። በመጨረሻም የፋሽስት በትር ልሳኗን ዘግቶ፣ ብዕሯን አዶልድሞ በመስከረም ወር 1969 ዓ.ም ቀብሯታል።

ጎሕ የካቲት 66ን ሕዝባዊ ንቅናቄ አስከትሎ ብቅ ያለች የያ ትውልድ ሀብት። ብዕሯ እንደ ጦር ከሕዝብ ጎራ ተሰልፎ አታግሏል። ለዴሞክራሲ መብትና ለሕዝብ መንግሥት ምስረታ በተካሄደው ፍልሚያ ታግላና አታግላ የድርሻዋን ተወጥታለች። ሕዝባዊነቷን ከፍ አድርጋ ለላብ አደሩና ለአርሶ አደሩ መብት ሞግታለች። ስለ ረሃብ፣ ድንቁርና፣ በሽታና ድህነት ያገር ያለህ! ብላለች። በሰላማዊው ጎዳና የያ ትውልድን ብዕር አድምቃ አስነብባለች። ኢትዮጵያ በስነጽሁፉ፣ በሥዕሉ፣ በግጥሙ፣ በፈጠራ ችሎታ ብርቅዬ ልጆች እንዳሏት ምስክር ሆናለች። ዛሬም ከህሊና የማይጠፉ ቅላጼዎቿ የጠንካራ ትውልድ ቦግ ብሎ መክሰም ምስክርነቷን ይዛ ተቀምጣለች።

1969 ዓ.ም. መስከረም ወር ደርግ ኢሕአፓን ለማጥፋት ያወጣውን አዋጅ ተከትሎ የመጨረሻ ዕትሟን በዚሁ ወር አውጥታ ለአንዴም ለመጨረሻ የመጀመሪያዋ የጥቃቱ ሰለባ በመሆን አሸልባለች። ልሳኗ ተዘጋ። የፋሺዝም በትር አረፈባት። የጎሕ ብርሃን ጨለማ ወረሰው። ሁለት ዓመት ዳዴ ብላ ያልቦረቀችው ጎሕ በአጭር ተቀጨች። ዛሬ የልደቷን 41ኛ ዓመትና የሙት ዓመቷን 39ኛ ዓመት አብረን እዘክራለን። እናስታውሳለን። ጥለሽ ያለፍሽው የ24 ወራት እትሞችሽ ህያው አድርገውሻል። ከመቃብር በላይ ስምሽን አንስተዋል። ታሪክሽ ተዳፍኖ አልቀረምና 41 ዓመታት ወደ ኋላ ተጉዘን ብቅ አድርገንሻል። ያኔ ምን ብለሽ ነበር? ዛሬ ላይ ሆነን እንማርበት ዘንድ ለያ ትውልድ አካላትም ለአዲሱ ትውልድም ያወረስሽንን 24 አበባዎች ለአንባቢያን ስናቀርብ በደስታ ነው። በ«ያ ትውልድ ተቋም» ዳግም አብበሻል።

ጎሕ መጽሔት መታተም ከጀመረችበት ጥቅምት ወር 1967 ዓ.ም. ጀምሮ "ብዕራችን ምን ይላል፣ ይድረስ ለጎሕ እና ሰዎች ምን ይላሉ" በሚለው ዓምዱ የተለያዩ አስተያየቶችንና መልዕክቶችን አስተላልፋለች። በወቅቱ በነበረው "የዕድገት በህብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ" ዘማቾችን ከቤተሰቦች በማገናኘት ድልድይና መነጋገሪያ ስልክ ሆና አገልግላለች። "የአንድ ኢትዮጵያዊ መልዕክት" አምዱ ቁም ነገሮችን አስተላልፋለች። የሀገራችን ሴቶች በአስከፊው ፊውዳላዊ ሥርዓት የደረሰባቸውን ድርብ ጭቆናና መፍትሄውን "በተለይ ለሔዋን" በሚለው አምዱ ሥር አስተምራለች። አንቅታለች። "የወጣቶች ድርሻ" በሚለው አምዱ በርካታ ወጣቶችን ለትግሉ አበርክታለች። ስለ ጤና አስተምራለች፣ ስለ ምጣኔ ሀብት ትንተናዎች አቅርባለች። የስፖርት ዜናዎችን ሳታቋርጥ ዘግባለች።

ጎሕ ዕጹብ ድንቅ ካደረጓት "የሂስ መድረክ" እና "ከኪነ ጥበብ" አምዱ ምታቀርባቸው ልብወለድ ትረካዎችና ግጥሞቿ ነበሩ። በአንድ በኩል በመኢሶን አመራር አባል አቶ ኃይሌ ፊዳና በሌላ በኩል በአደፍርስ፣ ጌታቸው ዲባባና ሌሎች ይደረግ የነበረው የብዕር ጦርነት በብዙዎች ዘንድ ጎሕን ተናፋቂ ሲያደርጋት አውርሳ የሄደችው ይህ መድረኳ የትላንቱን በዛሬ አዕምሮና የዓለም ሁኔታ ምን እንደሚመስል ዳግም ልንመራመርበት በር ይከፍታል። የአቶ ኃይሌ ፊዳ "ጠቅላላ ውኸቮንብር በሂስ ስም" በአንድ በኩል በተቃራኒው የአደፍርስ "ማስተማር ወይስ ማደናገር"፣ "ከድጡ ወደ ማጡ" እና የጌታቸው ዲባባ "ወጣ ወጣና እንደ ሸንበቆ ተንከባለለ እንደሙቀጫ" መጣጥፎች ያኔ በጉጉትና በሽሚያ ሲነበቡ ዛሬ ምን ትዝታን ይቀሰቅሳሉ?

ቅላጼ የተላበሱ የጎሕ ግጥሞች ዛሬም ህያውነት ያላቸው ይገኙበታል። ለአብነት የፍትጉ "ድርቡ ሰንሰለት በአመጽ ይበጠሳል፣ አመጻሽ አመጼና ዮፍታሄ" እንዲሁም የእሳቱ ተሰማ "ፀጋዬ ብዕርህ" ፣ አበራ ገሙ፣ ከጭቁን ጋር ለትግል፣ ለጓድ ሞት አያለቅሱም" ይጠቀሳሉ። በተጨማሪ በመመላለስ የተገጠሙት "አምጻለሁ፣ እሰይ ጓዴ አምጪልኝ፣ አመጻሽ አመጼ

እና እሰይ ጓዴ ከሰማኽኝስ” ስሜትን ቀስቃሽና ኮርኳሪ ግጥሞች በርካታ እህቶቻችንን የትግሉ ተሳታፊ ብቻ ሳይሆን ጠንካራ አመራር ሰጪዎችን አፍርቷል። ኪነት ለመደቧ፣ ኪነት ለሴቶች፣ ኪነት ለወጣቶች በጎሕ ታይቷል። ተመስክሯል።

በበርካታዎች ዘንድ ከፍተኛን አድናቆትን ያተረፈውና በተለያዩ አካባቢዎች በቲያትር መልክ ለመድረክ የቀረበው የ1968 ዓ.ም. ወርሃ ነሐሴ ዕትም “ልብ ወለድ” አምድ ላይ የቀረበው “ቱሉ ፎርሳ” ትረካ ጎሕን እጅጉን አስዋባት፣ አደመቃት። የላብ አደሩን ብሶት ው...ው...ታዬ ብላ አስተጋባች። ላብ አደሩ አጨበጨበላት፣ የብዙሃን ማህበራት ክንዳችን አሏት፣ ወጣቶች አዜሙላት፣ ፀሐፊዎች “ጎሕ የነቃች አንቂ” ብለው ገጠሙላት።

በወቅቱ ከነበረው የርዕዮተ ዓለም አሰላለፍ አንፃር ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር ለመላቀቅና ለሶሻሊዝም ሥርዓት ግንባታ ለተደረጉ ተጋድሎዎች “በልዩ ዕትም” አምዱ ጎሕ ስለ “ካርል ማርክስ እና ፍሬድሪክ ኤንግልስ፣ ሌኒን፣ ማኦ ሴ ቱንግ፣ ሆቺ ሚን፣ አሚልካር ካብራል፣ ጆዜፍ ስታሊን፣ ቹ ኤን ላይ፣ ጆርጅ ዴሞትሮቭ፣ አርነስቶ ቼ ጉቬቨራ፣ ላይላ ካሊድ፣ ቹ ቴህ፣ አንቶኒዮ ግራምሺ” የመሳሰሉት ታሪክና ተጋድሎ አስነብባ አልፋለች።

ጠቅለል ባለ መልኩ ከ”ፍፁም ነው እምነቴ” መጽሐፍ ስለ ጎሕ መጽሔት ከተፃፈው እንዋስና

*“የ “ጎህ” መጽሔት መልዕክት ከልባሷ የመጀመሪያ ሥዕል ጀምሮ ቅላጼንና ድምጽን በተላበሱ ቃላቷ በምታቘጎደጉዳቸው ግጥሞች እየታጀበች የምታስነብባቸው ጥናታዊ ጽሁፎችና ቅስቀሳዎች አልጠገብ አሉ። ጎህ እንደስሟ የዕውቀት ብርሃን፣ የተስፋ ብርሃን፣ ቀዳጅ ጎህ ሆነች።”* ፍፁም ነው እምነቱ ገጽ 95።

በዚህ አዲስ ዓመት የመጀመሪያ ዕትማችን የጎሕ መጽሔትን 41ኛ ዓመት ልደት እያከበርን 24 ልጆች ወልዳ ገና በዳዴነት እያለች መስዋዕት የሆነችበትን 39ኛ ዓመት ወርሃ መስከረም 1969 ዓ.ም. እንዘክራለን።

እንሆ ! ጎሕ ገፀ በረከትሽ በያ ትውልድ ድረ ገጽ ሥፍራቸውን ይዘው ለትውልድ ይተላለፉ ዘንድ ሠራን።


ጎሕን ስናነሳ ሁለት እህቶቻችንን ከፍ አድርገን ልናስቀምጥ ወደድን። አንደኛዋ “በዕንባዬ ውስጥ ተቀመጥ” ብላ እንደገጠመችው “በጎሕ ውስጥ ተቀመጭ” በማለት ስናስታውሳት፣ ሌላኛዋ “ሞተሽ መኖር ስታውቂበት” የተባለላትን “የተዳፈነው እሳት” በብዙዎች ልብ መኖሩን እንመሰክርላታለን።

የጎሕ መጽሔት ምክትል አዘጋጅ በመሆን አገልግላለች። ጎሕን ተወዳጅ፣ ተናፋቂና ተነባቢ በማድረግ ትልቁን ሚና የተጫወተችው መዝገብነሽ አባዩ ደስ ይበልሽ ስምሽ በጎሕ ከፍ አለልሽ እንላለን። የመዝገብነሽ አብዩ “ዕምባዬ ውስጥ ተቀመጥ” ግጥም እራሷ እንዳነበበችው ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ http://yatewlid.com/poem%20page.htm

ደርግ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ወደ 750 የሚሆኑ ሠራተኞችን በተፈላጊነት ከነምስላቸው ከአወጣቸው ወገኖች ውስጥ በ652ኛ ተራ ቁጥር የነበረችው የኢሕአፓዋ ጀግና መዝገብነሽ

አባዩ ነበረች። ወደፊት በከተማም፣ በአሲምባም የትግል ታሪኳን ለማቅረብ ቃል እየገባንና እዚህ አሜሪካ ከመጣች በኋላም ዘግናኝና አሳዛኝ አሟሟቷን ለማስነበብ እንሞክራለን።

መዝገብነሽ በነሐሴ 1967 ዓ.ም. የኅሕ ዕትም "የትግል ታሪክ አይሞት" በሚል በስሟ ከፃፈችው ለመታሰቢያነት በወቅቱ ካስነበበችው ጠቅሰን እናስነብብ ፦




# የትግል ታሪክ አይሞት

በጸደይ መጽሔት « ሞረሽና ልዩ እትማቸው » በሚል አቶ ክብሩ ይስፉ ሞገስ ለጻፉት መልስ ፤

ከመዝገብነሽ አባዩ ፤



632. መዝገብነሽ አባዩ
ነሕ መጽሔት ም አዘጋጅ



ስለኔ ስም መጨነቅዎ ግን በጣም አሳዝኖኛል ። በፍለጋ ስለተንከራተቱ በጣም ይቅርታ ። ግን ማወቅ የሚገባዎት ቁም ነገሩ የኔና የርስዎ ስም አይደለም ። የኔ ልዩ እትም መጻፍ የእርሱዎም ሂስ መቅረብ አለበት ። ታሪኩ ግን ከእውነቱ ወይ ፍንክች ። አብዮታዊ ታሪክን ማውገርገር የትግል መንገድን ማወላገድ በቁርጠኛ ታጋዮች ጠለላ ተለጥፎ ማምታታት ያልሆነውን እንደነበር አስመስሎ መቅጠፍ በታሪክ ፊት አንገት ያስደፋል ።

ደርግ የዓፄውን አገዛዝ በቁጥጥሩ ስር ባደረገ በጥቂት ወራት ውስጥ ጥናትና በቂ ዝግጅት ሳይደረግበት የአወጀው "የዕድገት በህብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ" በተለያየ መልኩ የበርካታ ወጣቶችን ሕይወት ቀጥፏል።

ሐምሌ 11 ቀን 1968 ዓ.ም. የወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ "ታጋይ ይሞታል እንጂ ትግል አይሞትም" በሚል ርዕስ እንደዘገበው "የዕድገት በህብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ የመጀመሪያው ዙር በተግባር ላይ ከዋለ ጊዜ አንስቶ ከሃምሳ ሰባት ሺህ ዘማቾች መካከል በግዳጅ ላይ እንዳሉ፤ በአድኀሪያን ጥይት፣ በልዩ ልዩ አደጋና በሕመም የሞቱት ዘማቾች ቁጥር 116 ነው።…" በማለት የሞቱትን ከነፎቷቸው በማውጣት ዘግቧል። በዚህ የአዲስ ዘመን ዕለታዊ ጋዜጣ ዘገባ ያልተካተቱ በርካታዎች እንደነበሩ ይታወቃል። ከነዚህም አንደኛዋ በዘመቻ ጣቢያዋ ላይ እንዳለች በአድኀሪያን የተቃጠለችው ዘማች መሠረት ሺፈራው ናት።

በወርሃ ነሐሴ 1968 ዓ.ም. የኅሕ ዕትም ከአንድ ጓዱ "ዋ መሠረት" በሚል ለማስታወሻ የተገጠመላትን እነሆ። "ዋ መሠረት ! ሞተሽ መኖር ስታውቂበት" እንዳለው ገጣሚ በኅሕ ውስጥ አብቢ እንላለን።

(በዘመቻ ላይ እንዳለች በአድሃሪ ለተቃጠለችው ለመሠረት ሽፈራው ማስታወሻ . . .)

**ዋ መሠረት** ! (ከአንድ ጓዱ)

ለድክመትሽ ካቀዱብሽ
ከአሽንክላ ከወጥመድሽ
በሸር ሴራው ላይ መጥቀሽ
ለትግሉ ጥቅም ነጥቀሽ
በገዛ ጠራቸው ወግተሽ
ዋ መሠረት ! ዋ መሠረት !
ሞተሽ መኖር ስታውቂበት
መሠረቷ. . . . . . . . መሠረቴ
ቃጠሎሽ የልብ እሳቴ
የአመፃ ነዳጅ ትውስቴ
ለትግል ሰደድ ሕይወቴ
የእንስት ኃይል ክስቴ
ዛሬም ነገ እሸቴ
ጥንቅሽ የድል. . .ማር. . . ወተቴ
የአርሶ. . . አደር የድርጅት ጣት
የእሳት ፍቱን ቀለበት
የጐጆውም የፍም እምብርት
ሥጋ. . . ሞገድ የቋያ እትብት
ለከራሚ ቁስል. . . . ሽረት
ኖሮ እማይገኝ ክብረ - ሞት
ሞተሽ ለጭቁን ትፍስሕት
ረግፈሽ ለምዝብር በእምነት
ለተገፉት ምድረ - ገነት
ልዕለ - ድል ሕያው ሐውልት።

ካንቺ ቤት ነው ካንቺ አካላት
እሳት . . . . . እሳት ያገኘበት
ዋ መሠረት ! ዋ መሠረት !
ሞተሽ መኖር ስታውቂበት
ፈለግሽ ጠርቶኛል ወይታዬን ስሚኝ እህት
በትግል የምሥራች አልኩ፣ ምሥር ብላ በይኝ
ጓዲት !
የነደድሽበትም እሳት
ላይተወኝ ሳውቅ ነቅቼበት
ካንቺ ተምሬ በሰልኩበት
ተያያዝኩኝ ተላመድኩት
ተቃጥዬ ላጋይበት
ተለብልቤ ላከስልበት
ዋ መሠረት ! ዋ መሠረት !
ሞተሽ መኖር ስታውቂበት
ካንቺው ቤት ነው ፡ ካንቺ አካላት
እሳት . . . . . . . .እሳት ያገኘበት
ዳር እስከ ዳር ሕያው እሳት

ዋ መሠረት ! ዋ መሠረት !

«ያ ትውልድ ተቋም» የመረጃ ምንጭ !

**ዋቢ ማጣቀሻ፡**

- ነሲቡ ስብሐት፡ "ፍፁም ነው እምነቴ" ቀይ ሽብር የከፍተኛ 15 እውነተኛ ታሪክ፤ መስከረም 2007 ዓ.ም. ሰሜን አሜሪካ።
- የኅሕ እትሞች ጥቅምት 1967 ዓ.ም. - መስከረም 1969 ዓ.ም.

መስከረም ፫ ቀን ፪ ሺህ ፰ ዓ.ም.
(September 14, 2015)

**«ያ ትውልድ ተቋም»**
ድረ ገጽ ፡ www.yatewlid.org, www.yatewlid.com
ኢሜል ፡ yatewlid@yahoo.com, yatewlid@gmail.com, yatewlid@hotmail.com

**የያ ትውልድ ተቋም Video ቅንብር እዚህ ተጭነው ይመልከቱ**
https://www.youtube.com/watch?v=t-zUE1nz11A

